የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ		
I አጠቃላይ መግለጫ		
የመስሪያ ቤቱ ስም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት
ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ቤተሰብ ጤና ፕሮፌሽናል III	የህብረተሰብ ጤና
	በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር.ቢሮ ብቻ የሚሞላ	
የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ/ተጠሪነት	የሥራው ደረጃ	የሥራው ኮድ
	XIII	
መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ		
በየደረጃው ባሉ ጤና ተቋማት		

II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡-

- ለጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ፣ ከፍተኛ የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት፣ በፈውስ ሕክምና አገልግሎት ለሕሙማን በምርመራና ሕክምና በማድረግ፣ በተሀድሶ ሕክምና ለአካላዊ ጉዳተኞችና ህሙማን ድጋፍና ክብካቤ በማድረግ፣ በመከላከል ሕክምና ጤናን በማጎልበት እና በሽታን በመከላከል በበሽታ የተጠቁ ህሙማንን እና የድንገተኛ አደጋ ጉዳተኞች ስቅይ መቀነስ፣ ወደ ጤናማ ኑሮአቸው መለሰስ፣ ሞትና አካል ጉዳትን በመቀነስ፣ ንቃተ ጤና በማበልፀግ፣ የበሽታን ስርጭት በመከላከል የሕብረተሰቡን ጤና ማሻሻል ነው።

2.2. ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

ውጤት **1**፡ ለጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ

- ለጤና ኤክስቴሽን ባለሙዎች የሙዊ ድጋፍ (ሱፐርቫይዝ) ለማድረግ የድርጊት መረሀ ግብር ያዘጋጃል፣ ቼክ ሊስት ያወጣል፣ ባለሙዎቹ የዕቅድ አፈፃፀም ውጤት ሪፖረትና የቁሳዊ ግብአት መረጃ ያደራጃል፣
- የሙዊ ድጋፍን (ሱፐርቫይዝ) ባዘጋጀው ቼክሊስት መሰረት ቃለ መጠይቅ ይጠይቃል፣ ውይይት ያካሂዳል፣ መልካም አፈፃፀምን ያበረታታል፣ ውስልነቶችን በመለየት ያሉትን የዕውቀትና ክህሎት ክፍተቶችን ይሞላል፣
- የስራ ክንውኖችን እየተዘዋወረ ይመለከታል፣ መዛግብት፣ ማህደርና ሰነዶችን ይመረምራል፣ መልካም አያያዞችን ያበረታታል፣ ውስንነት ያለባቸውን ይለያል፣ የዕውቀትና ክህሎት ክፍተቶችን ይሞላል፣
- በጤና ኬላ፣ በመኖሪያ ቤት፣ በመንደርና በቀበሌው የሚገኙ ባለድረሻ ተቋሚት እየተዘዋወረ ይጎበኛል፣ ቃለ መጠይቅ ያደርጋል፣ መልካ ተሞክሮዎችን ያበረታታል፣ ዕውቅና ይሰጣል፣ ያወያያል፣ የአድቮኬሲ ስራዎችን ይሰራል፣ በቅንጅታዊ አሰራር የጋጠሙ

ችግሮች ካሉ በውይይት እንዲፈቱ ያደርጋል፣

- ሙያዊ ድጋፉን አስመልክቶ የቃልና የፁሁፍ ግብረ መልስ ይሰጣል፣ አጠቃላይ ሪፖርት ያዘጋጃል፣ በዕቅድ አፈፃፀም ክፍተት ላይ የተከሰቱ የሥራ መርጃ ቁሳቁሶችና የብቃት ችግሮችን በመለየት ሪፖርት ያርጋል፣

ውጤት **2**፡ የስራ ላይ ስልጠና መርጃዎች ማዘጋጀትና ክፍተኛ የአሰልጣኖች ስልጠና መስጠት

- በሙያዊ ድጋፍና በተለያዩ ሪፖርቶች ከብቃት ውስንነት ጋር የተያያዙ የአፈፃፀም ውስንነቶች የያዙ መረጃዎችን በማደራጀት ይፈትሻ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የብቃት ውስንነቶችን ይለያል፣
- የተለዩ የብቃት አሃድን መሰረት ያደረገ መጠይቅ በማዘጋጀት የስልጠና ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፣ የጥናቱን ውጤት ይተነትናል፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆኑ የብቃት አሃዶችን ይለያል፣
- በተለየው የብቃት አሃድ መሰረት ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር በመሆን የስልጠና መርጃ የአመቻቾችና የተሳታፊ መመሪያ ያዘጋጃል፣ የመመሪያን አሰሪነት ለመወሰን በመስክ ላይ ሙከራ ያደርጋል፣ ማሻሻያ ሃሳቦች ከተገኙ በማካተት የስልጠና መርጃዎቹን እንዲጠናቀቁ ያደርጋል፣
- በተዘጋጀው የአመቻችና የተሳታፊ መመሪያ መሰረት የቅድመ ስልጠና ፈተና ይሰጣል፣ የፈተናውን ውጤት ይተነትናል፣ በስልጠና አጋዥ መመሪያ መሰረት ስልጠናውን ያካሂዳል፣ ስልጠናው ሲጠናቀቅ የድህረ ስልጠና ፈተና ይሰጣል፣ የፈተናውን ውጤት ይተነትናል፣
- በስልጠናው ሂደት ላይ በጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችና በአመቻቾች ክህሎትና ላይ የተሰጡትን አስተያየቶች ታሳቢ ያደረገ አጠቃላይ ሪፖርት ያዘጋጃል፣ በቀጣይ በሚያካሂደው ድህረ ስልጠና ዳሰሳ ጥናት የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጃል፣

ውጤት **3**፡ በፈውስ ሕክምና አገልግሎት ለሕሙማን ምርመራና ሕክምና ማድረግ

- በአጣዳፊና አዝጋሚ በሽታ የተያዙ ህሙማን ይጎበኛል፣ የተለያዩ የምርመራ ስልቶችን በመጠቀም ስለሕመሙ ሁኔታ ሙሉ ቃል ይቀበላል (history taking)፣ የሰውነት አሰራር ወሳኝ ምልክቶች ይለካል (measure vital sign)፣ ሙሉ የሰውነት አካላት ምርመራ (physical examination) ያደርጋል፣
- የህሙማን የምርመራና ህክምና መረጃ ይተነትናል፤ ተጨማሪ የላቦራቶሪ ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ ቀለል ያሉ የምርመራ ናሙናዎች ይወስዳል፣ ከህመምተኛው ሁኔታ በመነሳትና በተገኙ የምርመራ ውጤቶን መሰረት በማድረግ የሕመምተኛውን የበሽታ ሁኔታ ይለያል፣
- አስቸኳይ የሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ይለያል፣ ህክምና ይሰጣል፣ ከአቅም በላይ የሆነ የጤና ችግር ያማክራል፣ ለከፍተኛ ምርመራና ሕክምና ከፍ ወደአለ ጤና ተቋም ያስተላልፋል፣
- ለሕሙማን በመርፌ ወይም በአፍ የሚሰጡ መድሃኒቶችን ያዛል፣ የህመሙን ሁኔታ ይከታተላል እንደአስፈላጊነቱ የህመም ደረጃውን እያጠና እያማከረ መድሀኒት ይለውጣል፣ በተከታታይም ለህሙሙ ቤት ለቤት የጤና ክብካቤ ያደርጋል፣
- ለሕሙማን በደም ስር የሚሰጡ የሰውነት መተኪያ ፈሳሽና ንጥረ ነገር ይሰጣል፣ በቤት ውስጥ ሊደረግ ስለሚገባ የጤና ክብካቤ

ለህመምተኛውና ለቤተሰቡ ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል፣

- የህክምና አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ለሚደርሱ ድንገተኛ ጉዳትና ሕመም ሆነ ህክምናው ያስከተለውን ጎናዊ ጉዳትን ላይ የድንገተኛ ሕክምና ዕርዳታ ይሰጣል፣ በጉዳተኛ ማስተላለፍ ላይ ከጤና ጣቢያና ከሆስፒታል ትሪያጅ ተቀናጅቶ ይሰራል፣

ውጤት **4**፡ በተሀድሶ ሕክምና ለአካላዊ ጉዳተኞችና ህሙማን ድጋፍና ክብካቤ ማድረግ

- የተሃድሶ ህክምና አስመልከቶ በተለያዩ የህክምና ሂደት ያለፉና በሕይወት ዘመናቸው ከሆስፒታል የተሃድሶ ሕክማና እስከ ማህበረሰብ ተኮር የተሃድሶ ድጋፍና ክብካቢ የሚያስፈልጋቸውን ተገልጋዮች ይለያል፣
- በተሃድሶ ሕክምና ድጋፍና ክብካቤ ከሚሰጠቻው ባለሙያዎች መካከል የደረሰባቸው የአካል ጉዳት አይነትና ደረጃ ይለያል፣ የአካል ጉዳቱ ደረጃ የሚሻሻልና የመሻሻል ውስንነት ያለባቸውን ሁኔታዎች ይዘረዝራል፣ ይተነትናል፣
- በተሃድሶ ሕክምና የህሙማንን አጠቃላይ የጤና፣ የማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ታሪክ ያጠናል፣ በጥናቱም ተመስርቶ የአካል ጉዳት የችግሩን ኢላማ ይለያል፣ የአካል ጉዳት ማሻሻያ ስልትና ዘዴ ይቀይሳል፣
- ለአካል ጉዳተኞች በተገኙት ችግሮችና ማሻሻያ ዘዴዎች ላይ ተመስርቶ የተሀድሶ ሕክምና የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጃል፣ አስፈላጊ ግብአትና እንዲሟላ ያደርጋል፣ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ይተገብራል፣
- የሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ እንዲሁም የሰውነት ማንቀሳቀሻ መርጃዎች እንደ ክረንችና ዊልቸር ተጠቃሚ ያደርጋል፣ አካለዊና መንፈሳዊ ጥንካሬ እንዲያዳብሩ ትምህርት ይሰጣል፣ ለሰውነታቸው ምቾትና ድጋፍ በሚሰጣቸው ዘዴዎች ላይ ስልጠና ይሰጣል፣
- አካል ጉዳተኞች የኦርቶፔዲክ ፊዚዮቴራፒ ህክምና እንዲያገኙ ያደርጋል፣ በጤናማ የአኗኗር ዘይቤ ላይ ሙያዊ ምክር ይሰጣል፣
- ለህሙማን ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ ለቤተሰቦችና በጎ ፈቃድ ተባበባሪዎች በጉዳዩ ዙሪያ ያላቸው አስተዋፆ ያሳውቃል፣ ለአካል ጉዳተኞች በሚደረግላቸው ድጋፍና ክብካቤ ላይ አቅማቸውን ያጎለብታል፣
- ማህበረሰብ አቀፍ የተሃድሶ አገልግሎት ከጤና ኤክስቴሽን ፕሮግራም ጋር ያቀናጃል፣ በተሃድሶ ሕክምና ድጋፍና ክብካቤ ላይ የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ውጤቱንም በመገምገም የማሻሻያ ስልት ይቀይሳል፣
- የተሃድሶ ህክምና የድርጊት መርሀ ግብር አፈፃፀም ውጤት በየወቅቱ በመገምገም ለአካል ጉዳተኞች በሚሰጠው ድጋፍና ክብካቤ ላይ የማሻሻያ ስልቶችን ይቀይሳል፣ በአካል ጉዳተኛ ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር በትብብር ይሰራል፣

ውጤት **5**፡ በመከላከል ሕክምና ጤናን ማጎልበት እና በሽታን መከላከል

- በጤና ኤክስቴሽን ፕሮግራም ላይ በህብረተሰብ ክፍሎችና በተቋማት ያለን የባለደርሻ አካላት ሚና ይፈትሻል፣ ከፍተኛ የአድቮኬሲ ስራዎች ይሰራል፣ በከፍተኛ ጉዳዮች ላይ የማህበረሰብ ንቅናቄና ያካሂዳል፣
- በመሰረተ ጤና ክብካቤ ዙሪያ ጭብጦችንና መልዕክቶችን ያዘጋጃል፣ የመስክ ላይ ሙከራ ያደርጋል፣ ከሙከራ የተገኙ ጉዳዮችን በማካተት ያጠናቅቃል፣ በተለያዩ ብዙሃን መገናኛዎች በመጠቀም መልዕክቶች እንዲተላለፉ ያርጋል፣

- የሃይጂንና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ከፍተኛ ስራዎችን ያከናውናል፣ በአካባቢ ተመራጭ የሆኑ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ስርፀት ያካሂዳል፣
- የቤተሰብ ጤና ክብካቤ ታላሚዎችን የጤና አገልገሎት ፍላጎትን ይለያል፣ አማራጭ ስልቶችን ያመነጫል፣ ለከፍተኛ የጤና ክብካቤ ለተላኩትን ተጠቃሚዎች አገልግሎት ይሰጣል፣
- ተላላፊና ተላላለፊ ያልሆኑ በሽታዎችና ጉዳቶች መከላከልና መቆጣጠር ስራዎች ላይ ቤተሰብና ማህበረሰብ ተኮር አገልግሎት አሰጣጥ ስልቶችን ያወጣል፣ የመከላከልና መቆጣጠር ስራዎችን ያከናውናል፣
- ማህበረሰብ ተኮር የተቀናጀ በሽታዎች ቅኝትና ምላሽ ስርአትን ካለው የማህበረሰብ አደረጃጀት ጋር ተስማሚነት ይመረምራል፣ በየወቅቱ በማህበረሰቡ ሊለዩና ሪፖርት ሊደረጉ የሚችሉትን የተላላፊ በሽታዎች ባሕሪና ምልክት ያጠናል፣መስፈርት ያዘጋጃል፣ በወረርሽ በሽታዎች ቁጥጥር ስራን ያከውናል፣
- የሕሙማን ቅብብሎሽ ስርአት ከማህብረሰብ እስከ ጤና ተቋም የቅብብሎሽ ዕርከን መሪ ፍኖተ ካርታ ያወጣል፣ የድንገተኛ ጉዳትና ሕመሞች ደረጃና መስፈርት ያዘጋጃል፣ የቅድመ ሆስፒታል የሕይወት አድን ዕርዳታ ያደርጋል፣

III የሥራው ባህሪ መግለጫዎች

3.1 የሥራ ውስብስብነት

- ሥራው ለጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ የማድረግ፣ የስራ ላይ ስልጠና መርጃዎች የማዘጋጀትና ከፍተኛ የአሰልጣኖች ስልጠና የመስጠት፣ በፈውስ ህክምና አገልግሎት ህሙማን የመመርመርና የማከም፣ በተሃድሶ ህክምና አካለዊና መንፈሳዊ ድጋፍና ክብካቤ የማድረግ፣ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ ጤናን የማጎልበትና በሽታን የመከላከል ውጤትን ለማሳካት የሚከናወን ነው።
- ይህንን ሥራ በሚሰራበት ወቅት በሙያ ድጋፍ ያለማመን፣ ያለመተባበር፣ ግብረመልስ ያለመቀበል፣ በስልጠናው በተለያያ የመረዳት ደረጃ ላይ የመገኘት፣ ከተለያዩ ተሳታፊዎች ስልጠናውን የሚያውኩ ባህሪያት የማሳየት፣ የፈውስ ህክምና አገልግሎት የህሙማን ተለዋዋጭ የሕመም ስሜትና የበሽታው ውስብስብነት ምርመራውንና ሕክምናውን አስቸጋሪ የሚድረግ፣ የመድሀኒቶች የመፈውስ ኃይል መቀነስ፣ መድሐኒትን በአግባቡ ያለመውሰድና የማቋረጥ፣ የተሃድሶ ህክምና ሰው ስራሽ የአካል ደጋፊ ምርቶች ለሰውነት ምቹ ያለመሆን፣ የአኗኗር ዘይቤን የሚቀይርና ዕድሜ ልክ መጠቀም ላይ የመሰላቸት፣ የመከላከል ሕክምና ውጤቱ በአጭር ጊዜ ያለመታየት፣ የሰዎች ባሕሪን መለወጥ ፈታኝ የመሆኑ የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው።
- እነዚህን ችግሮችና ፈታኝ ሁኔታዎች ሲያጋጥም የመግባባት ክህሎት በመጠቀም የማሳመንንና ተባባሪ የማድረግ፣ የተለያዩ የስልጠና ዘዴዎችን በመጠቀም፣ የሰልጣኞችን ባሕሪ ማረሚያ መርሆና ስልት በመጠቀም፣ ህሙማንን በተለያየ ሁኔታ ቀርቦ በማወያየት፣ የተለያዩ የምርመራ ዘዴዎች በመጠቀም፣ የምርመራ ውጤቶችን ከተለያዩ ሁኔታዎች ጋር በመተንተን፣ መድሀኒቶችን አይነትና ወደ ሰውነት የሚገቡበትን መንገድ በመለዋወጥ፣ ሕሙማንን ከመድሀኒት ጋር ቁርኝነት እንዲፈጥሩ ተከታታይ የምክር አገልግሎት በመስጠጥና በማሳመን፣ የአካል ደጋፊ ምርቶች ይበልጥ ተስማሚና ምቾት ሰጪ አጠቃቀም ላይ የክህሎት ስልጠና በመስጠጥ፣ ዘላቂ ጤናማ ሕይወት አኗኗር ክህሎትን በማበልፀግ፣ የመከላከል ሕክምና ላይ በተከታታይ ግንዛቤ በመፍጠር፣ የተገኙ መልካም

ተሞክሮውችን በመፍትሄነት በመጠቀም ያልተወቀ ሁኔታን ተከትለው የሚመጡ ሁኔታዎችን በመተርጎምና በመተንተን ወይም በመገምገም የሚከናወን ነው።

3.2 ራስን ችሎ መስራት

3.2.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ

- ሥራው የሙያዊ ድጋፍ መረጃ የአተገባበር መመሪያ፣ የአመቻችንና የተሳታፊ መመሪያ፣ የህክምና አሰጣጥ ፕሮቶኮልን፣ የአተገባር የስራ ሂደትና የተግባራ ቅደም ተከተል የፍሰት አመላካችን፣ የህክምና መርጃ መሳሪያዎችን፣ በስራ ላይ ፈጣን ማጣቀሻዎችን፣ የአሰራር ደንብና መመሪያ መሰረት በማድረግ ይከናወናል።

3.2.2 ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ

- ሥራው የቤተሰብ ጤና የመንከባከብ ሥራው ተፈላጊውን ቤተሰባዊ ጤና ከማምጣትና ተፈላጊውን ግብ ከመምታት አንጻር እንዲሁም በአጠቃላይ ከጤና ሥራዎችና ከመከላከል ስትራቴጂዊ ጋር ካለው ውህደት አንጻር ግምገማ ይደረግበታል።

3.3 ተጠያቂነት

3.3.1 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት

- ሥራው ሙያዊ ድጋፍ የማድረግ፣ የስራ ላይ ስልጠና መርጃዎች የማዘጋጀትና ከፍተኛ የአሰልጣኞች ስልጠና የመስጠት፣ በፈውስ ህክምና አገልግሎት ህሙማን የመመርመርና የማከም፣ በተሃድሶ ህክምና አካለዊና መንፈሳዊ ድጋፍና ክብካቤ የማድረግ፣ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ ጤናን የማጎልበትና በሽታን የመከላከል ውጤትን ለማሳካት የሚከናወንበት በመሆኑ ይህ ስራ በሚፈለገው ደረጃና ጥራት ባይከናወን ወይም በሥራ ክንውን ወቅት የሚከሰቱ ስህተቶች በወቅቱ ባይታሙ በስራ ላይ ያሉ ባለሙያዎች ለስራ አለመነቃቃት፣ በቅድመ አገልግሎት የተገኘ ዕውቀትና ክህሎት በመረሳት በስራ ላይ ስህተት የመፈጠር፣ የጥራት መውረድ ሊያስከትል ይችላል፣ ሕሙማንና አካል ጉዳተኞች ለከፋና ለተወሳሰበ የህምምና ጉዳት እንዲሁም ለሞት ደረጃ ሊያደርስ ይችላል፣ የበሽታዎች ስርጭት በመስፋፋት በወረርሽ መልክ የመከሰት አጋጣሚ በመፍጠር ሕብረተቡን ለከፋ ህመምና ሞት ሊያደርስ ስለሚችል ለተገልጋዮች የሚሰጠውን አገልግሎት በማስተጓጎልና ቅሬታን በመፍጠር በተቋሙ ዕቅድ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል።

3.3.2 ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ

- ሥራው የስልጠና ቅድመና ድህረ ስልጠና ፈተና በጥንቃቄ የሚያዝበት በመሆኑ፣ የሕሙማን የግል የህክምና ታሪክና የተገልጋዮች የጤና መረጃ በሚስጠር የሚያዝበት በመሆኑ መረጃው ለማይመለከተው አካል ተላልፎ ቢሰጥ በባለሙያውና በሕክምናው ክፍሉ

ታአማኒነትን ሊያሳጣ በባለሙያውና በተገልጋች መካከል ከፍተኛ ቅራኔና አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል።

3.4 ፈጠራ

- ሥራው የተለያዩ የስልጠና ዘዴዎችን በመጠቀም፣ የስልጣኞችን ባሕሪ ማረሚያ መርሆና ስልት በመጠቀም፣ ህሙማንን በተለያየ ሁኔታ ቀርቦ በማወያየት፣ የተለያዩ የምርመራ ዘዴዎች በመጠቀም፣ የምርመራ ውጤቶችን ከተለያዩ ሁኔታዎች ጋር በመተንተን፣ መድሀኒቶችን አይነትና ወደ ሰውነት የሚገቡበትን መንገድ በመለዋወጥ፣ ሕሙማንን ከመድሀኒት ጋር ቁርኝነት እንዲፈጥሩ ተከታታይ የምክር አገልግሎት በመስጠጥና በማሳመን፣ የአካል ደጋፊ ምርቶች ይበልጥ ተሰማሚና ምቾት ሰጪ አጠቃቀም ላይ የክህሎት ስልጠና በመስጠጥ፣ ዘላቂ ጤናማ ሕይወት አኗኗር ክህሎትን በማበልፀግ፣ የመከላከል ሕክምና ላይ በተከታታይ ግንዛቤ በመፍጠር፣ የተገኙ መልካም ተሞክሮውችን በመፍትሄነት በመጠቀም አማራጮች በማቅረብን የሚጠይቅ ነው።

3.5 የሥራ ግንኙነት

3.5.1 የግንኙነት ደረጃ

- ሥራው በመ/ቤት ከውስጥ ከጤና ኤክስቴሽን ባለሙዎች፣ ከሱፐርቫይዘር፣ ፕሮግራም አስተባባሪዎች፣ ጽ/ቤት ኃላፊ፣ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች አስተባበሪዎችና ባለሙያዎች፣ ከውጪ ከሕሙማን፣ ከአስታማሚ ቤተሰቦች፣ ከተገልጋይ ሕብረተሰብ፣ ከቀበሌ አመራር፣ መንግስታዊና መንገስታዊ ካልዎኑ ተቋማት ፕሮግራም አስተባበሪዎች ጋር ግንኙነት ማድረግን የሚጠይቅ ነው።

3.5.2 የግንኙነቱ ዓላማ

- ሥራው ለማሰልጠን፣ ለማብቃት፣ ለመግባባት፣ የሕሙማን ለመመርመር፣ መረጃ ለመስጠንና ለመቀበል፣ መድሀኒት ከመውሰድ፣ የሰውነት ድጋፍ ከመጠቀነም፣ የባህሪ ለውጥ ከማምጣት አንፃር በተደጋጋሚ የሚነሱ ጉዳዮችን ግልፅ በማድረግ ለመደራደርና ለማሳመን፣ የሕሙማን፣ የባህሪና የበሽታ ሁኔታዎች ለመከታተል፣ ከግለሰብ፣ ቤተሰብና ማህበረሰብ ጋር ተወያይቶ ለመግባባት፣ ተስማምቶ በመስራት አንድ ውጤት ላይ ለመድረስ የማግባቢያ ክህሎት የሚጠይቅ ነው።

3.5.3 የግንኙነቱ ድግግሞሽ

- ሥራው የሥራ ግንኙነት ድግግሞሽ ከሥራ ጊዜው 75 ከመቶ ይወስዳል።

3.6 ኃላፊነት

3.6.1 ኃላፊነት ለሰው ሀብት

3.6.1.1 በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት

- የለበትም

3.6.1.2 የኃላፊነት ዓይነትና ደረጃ

- የለም

3.6.2. ኃላፊነት ለንዋይ

- የለም

3.6.3 ኃላፊነት ለንብረት

- ሥራው ኮምፒውተር፣ ተዛማጅ የኤሌክተሮኒክስ ውጤቶች፣ የፈውስ፣ የተሃድሶና የመከላከል ሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚረዱ የክትባት መድሐኒቶች N፣ የማዋለጃ መሳሪያዎች፣ የክትባት መድሀኒት ቅዝቃዜ መጠበቂያ /ፍርጅ/፣ የ mjm¶Ã HKMÂ XRÄ¬ mSÅ መሳሪያዎች ½ የስራና የትምህር ማጣቀሻዎች፣ ኦዶቪዥዋል መሳሪያዎች፣ ኤሌክትሮኒክስ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎ፣ ወንበር፣ ጠረ p&ዛና መደርደሪያ ጠቅላላ ግምታቸው ብር 80,000 (ሰማንያ ሺህ) የሚደርሱ ቋሚ፣ አላቂ ዕቃዎችን ተረክ ï በአግባቡ የመያዝና የመጠቀም ኃላፊነት አለ b ት።

3.7 ጥረት

3.7.1 የአዕምሮ ጥረት

- ሥራው ለጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ የማድረግ፣ የስራ ላይ ስልጠና መርጃዎች የማዘጋጀትና ከፍተኛ የአሰልጣኖች ስልጠና የመስጠት፣ በፈውስ ህክምና አገልግሎት ህሙማን የመመርመርና የማከም፣ በተሃድሶ ህክምና አካለዊና መንፈሳዊ ድጋፍና ክብካቤ የማድረግ፣ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ ጤናን የማጎልበትና በሽታን የመከላከል ውጤትን የሚከናወንበት በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የአእምሮ ጥረት በተከታታይ የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከሥራው ጊዜ 75 **በመቶ ይወሰዳል።**

3.7.2. ስነልቦናዊ ጥረት

- ***ሥራው በሙያዊ ድጋፍ ላይ የሚነሳ ጭቅጭቅ፣ አለመግባባት፣ በስልጠና ላይ ሂደቱን የማወክ፣ አሰልጣኝን የመፈታተን፣ ሰልጣኞች በተለያዩ የዕውቀትና ክህሎት ደረጃ ላይ መገኘት፣ የህሙማንን የህመም ስቃይና የመዳን ጉት፣ የአስታማሚን***

ቤተሰብ ጭንቀትና መረበሽ፣ የአካል ጉዳተኛ ስነልቦናዊ ቀውስ፣ የግለሰብ፣ የቤተሰብና ማህበረሰብ ለጤና ማጎልበትና በሽታ መከላከል ስራ ተባባሪ ያለመሆን፣ መነታረክ ችሎና ተገንዝቦ ውጤትና ለውጥን ለማምጣት የሚያስችል የሥራ ትጋትንና ቁርጠኝነትን፣ ሥነልቦናዊ መሰጠትንና ዝግጅነትን ላይ ከፍተኛ ጥረትን የሚጠይቅ ነው።

3.7.3 የዕይታ ጥረት

- ሥራው የታካሚዎችን የምርመራ ውጤት መተንተን፣ ሪፖርቶችንና ዕቅዶችን ማዘጋጀት የዕይታ ጥረትን የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከስራ ጊዜው 35 በመቶ የሚጠይቅ ነው።

3.7.4 የአካል ጥረት

- ሥራው ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት፣ የስራ ስልጠና ለማካሄድ፣ ከህሙማን ምርመራና ሕክምና፣ ከአካል ጉዳተኛ ድጋፍ ክብካቤ፣ የግለሰብ፣ የቤተሰብና ማህበረሰብ ጤና ከማጎልበትና በሽታ ከመከላከል አንፃር አስቸጋሪ መልክዓ ምድር አቀማመጥ ባላቸው ቦታዎች፣ ከመንደር ወደ መንደር/ከጎጥ ወደ ጎጥ፣ ቤት ለቤት ክረምት ከበጋ በእግር በመጓዝ እያንዳንዱን ቤት በመጎብኘት የሚከናወን በመሆኑ አጠቃላይ 30 በመቶ በእግር በመጓዝና ጎንበስ ቀና በማለት፣ 50 በመቶ በመቆምና 30 በመቶ በመቀመጥ የሚከናወን ነው።

3.8. የሥራ ሁኔታ

3.8.1 ሥጋትና አደጋ

- ሥራው ከመንደር ወደ መንደር/ከጎጥ ወደ ጎጥ፣ ቤት ለቤት በሚኬድበት ወቅት በውሻ የመነከስ፣ በመርዛማ ነፍሳትና እንስሳት የመነደፍ፣ ሴቶች የመደፈር፣ የመውደቅና የመሰበር፣ በስለታም ነገሮች የመወጋ T አደጋ የተጋለጠ ሲሆን ይህም ለተለያዩ አካላዊ ጉዳቶች ይዳርጋል።

3.8.2. የሥራ አካባቢ ሁኔታ

- ሥራው ሥራው ከመንደር ወደ መንደር/ከጎጥ ወደ ጎጥ፣ ቤት ለቤት ክረምት ከበጋ፣ ፀሀይ ሀሩርና ዝናብና ቅዝቃዜ፣ መጥፎ ሽታ፣ አቧራ፣ ጭስ፣ ተላላፊና ወረርሽ በሽታ በተከሰተበት፣ ባለበት አካባቢ የሚከናወን በመሆኑ በጤና ላይ በጣም ከፍተኛ መታወክ በማስከተል እስከሞት ሊያደርስ የሚችን የስራ አካባቢ ነው።

3.9. እውቀትና ክህሎት፣

3.9.1 ትምህርት

የትምህርት ደረጃ	የትምህርት ዓይነት

የመጀመሪያ ዲግሪ	ቤተሰብ ጤና

3.9.2 ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ

የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ	ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት		
6 ዓመት በመጀመሪያ ዲግሪ			
የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም	ፊርማ	ቀን	
የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	ፊርማ	ቀን